ሐምሌ 13 ቀን 2016 ዓ.ም

በአብክመ ፍትሕ ቢሮ ለዞን ፍትሕ መምሪያ ዐቃቤ ሕግ የደረጃ ዕድገት የተዘጋጀ የጽሑፍ ፈተና

የፈተናው መመሪያዎች

- ለመልስ መስጫነት በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ብቻ መልሰ ሊሰራ ይገባል፤
- የሚሰጡት መልስ ግልጽ፣ አጭር እና ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የሕግ ድንጋጌና ምክንያት መደገፍ ይኖርበታል፤
- ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክሩ፤
- ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ 3:00 ተመድቦለታል፤
- ፈተናው እንዲጀመር በፈተና አስፈጻሚዎች ሳይፈቀድ ፈተናውን መስራት የተከለከለ ነው፤
- በፈተና ክፍል ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ የሕግ ኮዶች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በስተቀር የሞባይል ስልክም ሆነ ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን እንዲሁም ማናቸውንም ዓይነት ጽሑፎችን፣ የሕግ ማብራሪያዎችንም ሆነ የሰበር ውሳኔዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፤
- ፈተናው በሚሰጥበት ሰዓት እርስ በእርስ መነጋገር ወይም በሌላ በማንኛውም አግባብ ከሌላ ተፈታኝ ጋር መነጋገር እንዲሁም ሕጎችን መዋዋስ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤
- ተፈታኞች በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ቅጽ (ወረቀት) በተገለጸው ባዶ ቦታ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ብቻ መ.ለ. ስማቸውን፣ የሚሰሩበትን ዞንና ሌሎች በቅጹ የተገለፀ መረጃዎችን መመላት አለባቸው።
- ፈተናውን እንደጨረሱ ከፈተና አዳራሽ ከመውጣትም በፊት በስም መቆጣጠሪያ ዝርዝሩ ላይ መፈረምዎን እንዲሁም የመልስ መስጫ እና የፈተና ወረቀቶችን መመለስዎን ያረጋግጡ።

መልካም ውጤት!

ጥያቄዎች

አቶ አለማየሁ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደሴ ቅርንጫፍ የደንበኞች አገልግሎት መኮንን ሆኖ ሲሰራ ከባንኩ መመሪያና አሰራር ዉጭ የባንኩ ደንበኛ ከሆኑት ወ/ሮ መሰረት አያሌዉ በቁጠባ ደብተራቸዉ የተቀመጠዉን ብር 35,320 (ሰላሳ አምስት ሽህ ሦስት መቶ ሀያ ብር) ከፈቃዳቸዉ ዉጭ አቶ አበበ በተባለ ግለሰብ የተከፈተ የቁጠባ ሂሳብ አስተላልፎ የተገኘ መሆኑን የባንኩ ኦዲተር አረጋግጧል። ባንኩም በጉዳዩ ላይ የወንጀል ምርመራ እንዲደረግ ለሚመለከተዉ የፖሊስ አካል አሳውቋል። ፖሊስም በደረሰዉ ጥቆማ መሰረት የሰነድ ማስረጃዎችን አሰባስቦና የምስክርነት ቃል ተቀብሎ ስለጨረሰ ሌላ የማሰባሰበዉ ማስረጃ አይኖርም፤ ለክሱ በቂ ማስረጃ ስብስቤያለሁ ብሎ ስላሰበ ቃል ለመቀበል አለማየሁን ይዞ በፖሊስ ጣቢያ አስሮት ይገኛል።

ሀ) አለማየሁ በዋስ የመዉጣት ሕገ መንግስታዊ መብቱን ለመጠቀም ፈልጎ የዋስትና ጥያቄዉን ለደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ቢያቀርበዉና ፍ/ቤቱም ዐ/ሕግን የዋስትና አስተያየት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል። እርስዎ መዝገቡ የደረሰዎት ዐ/ሕግ ቢሆኑ ለፍ/ቤቱ ምን አይነት አስተያየት ያቀርባሉ? ለምን? 5%

ለ) እንደ ዐ/ሕግ አለማየሁ ላይ የተጣራዉ የወንጀል ምርመራ መዝገብ ተጠናቆ ለእርስዎ ቢደርስ የትኛዉን የሕግ ድንጋጌ ጠቅሰዉ ክስ ይመሰርታሉ? ክሱስ ለየትኛዉ ፍ/ቤት ይቀርባል? ለምን? 5%

2. አቶ ማንደፍሮ ቢያዝን የካቲት 02 ቀን 2016 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8:00 አካባቢ ፍኖተ ሰላም ከተማ ልዩ ሰሙ ዳሞት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ይመኙሻል መንገሻን በቦክስ ሆዷን በመምታት ሆዷ ውስጥ የነበረውን የ6 ወር ጽንስ ቦታውን እንዲለቅ እና በሆዷ ውስጥ እንዲሞት በማድረግ ወ/ሮ ይመኙሻልን በድብደባው ምክንያት ለደም መርጋት እና ለደም መፍሰስ ዳርጓታል የሚል የምርመራ መዝገብ ከፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጽፈት ቤት የወንጀል ምርመራ የስራ ሂደት ለፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ደርሶት በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ለማሳረፍ ተችግሯል። እርስዎ የምዕራብ ጎጃም ዞን የዞን ዐቃቤ ህግ በመሆንዎ መሪ ትዕዛዝ ተጠይቀዋል። በመዝገቡ ላይ የሚሰጡት ውሳኔ ምን ይሆናል? 8%

3. በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት የአስተዳደር መሰሪያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባቢቶች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚችሉበት ሁኔታ አለ ብለው ያስባሉ? ለምን? 6%

4. አቶ አለሙ እና ወ/ሮ አስካል በመካከላቸው ያደረጉትን የቤት ሽያጭ ውል ተስተው በሽያጭ ውሉ መሰረት የገዛሁትን ቤት ሊያስረክቡኝ አልቻሉም የሚል ክርክር ተነስቶ በክርክሩ ፍ/ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩ እየተካሔደ ባለበት ሁኔታ አባይ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር እንዲሁም የሻጩ ወንድም እና የድሬ ዳዋ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ዘመነ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን በመጥቀስ ጣልቃ-ገብተው እንዲከራከሩ ያቀረቡትን ጥያቄ ተስተው ጥያቄያቸው ተቀባይነት ቢያገኝ የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስራክሮ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል ብለው ያምናሉ? ለምን? 6%

5. ጥቅምት 12/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ሲሆን በባህርዳር ከተማ አስተዳደር ስለ ከተማው ልማት ጉዳይ በከተማ አስተዳደሩ በኩል ነዋሪው ለስብሰባ እንዲገኝ በተላለፈው መልዕክት መሰረት ከተማ አስተዳደሩ ግቢ ውስጥ ስብሰባው እየተደረገ እያለ አቶ ሰሎሞን እና አቶ ኢሳያስ ስበሰባው እንዲበተን በማሰብ ስብሰባው ላይ በተገኘው ህዝብ ላይ ጥቃት እንከፍታለን በሚል ከስብሰባው መሃል ገብተው የተናገሩ በመሆኑ በአሉቱ የተደረገው ስብሰባ ተቋርጧል። በዚህም መሰረት ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾች ላይ የኢፌድሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 490/1/ መሰረት ክስ አቅርቦባቸዋል። ጥፋተኛ ሆነው በመገኔታቸው ዐቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ የፈፀሙት የወንጀል ክብደት እና የተከሳሾችን አደገኛነት በማመዛዘን በአስራት እና በመቀጮ እንዲቀጡለት ያሳሰበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የተከሰሱበት የህግ ድንጋጌ በአማራጭ ቅጣት ያስቀመጠ በመሆኑ በአስራት ቅጣትና በመቀጮ ተጣምሮ ሊቀጡ አይገባም በሚል የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ውድቅ በማድረግ ነገር ግን ከተከሳሾቹ አደገኛነትና ከወንጀሉ ክብደት አንፃር በመመዘን አስራት ቅጣቱን መርጦ ተከሳሾችን እያንዳንዳቸውን በ 4 ወር ቀላል አስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል። ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግን አስተያየት ውድቅ ማድረጉ ምን ያህል ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ? ለምን? 6%

6. በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ክስና መልሳቸውን ሲያቀርቡ አያይዘው ካቀረቧቸው ማስረጃዎች ባሻገር ሌሎች ማስረጃዎች ሊቀርቡ ከሚችሉባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ 3ቱን ጥቀሱ።6%

#በተለያየ ጊዜ የአብክመ ዳኞች ለከፍተኛ ፍ/ቤትና ለጠቅላይ ፍ/ቤት የተፈተኗቸው ጥያቄዎች!
1.የህገ መንግስቱን መሰረታዊ መርሆዎችን ዘርዝር።
2.በአጭር ሥነ-ሥርአት እና በተፋጠነ ሥነ-ሥርአት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ዘርዝር።
3.ፍርድ ቤት የራሱን ውሳኔ የሚያይባቸው ሁኔታዎች ምንምን ናቸው።
4.ይቅርታና ምህረት ልዩነቱ ምንድነው።
5.በአስገዳጅ ሁኔታ እና በህጋዊ መከላከል መሀከል ያለው አንድነት እና ልዩነት ምንድነው።
6.ቀብድ የተቀበለ ሰው ውሉን ለማቋረጥ ቢፈልግ ምን ማድረግ አለበት።
7.ሰራተኛ በራሱ ያለ ማስጠንቀቂያ ስራ ሊያቋርጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች መንድናቸው።
8.ሁለቱ አይነት የቅጣት ገደቦች አንድነት እና ልዮነት።የሚፈቀድባቸው እና የሚከለከልባቸው መንገዶችን አስቀምጥ።
9.በአስቸኳይጊዜ አዋጁ የማይታገዱ የህገ መንግስቱ አንቀጾች የትኞቹ ናቸው።
10.የውል መሰረዝ እና መፍረስ አንድነት እና ልዩነት።
11.ለመሰየም የሚፈቀድበት እና የሚከለከልበት መስፈርት።
12.አሰቦ እንድ ሰው ወንጀል አድርጎ የማይቀጣው መቼ ነው።
13.ፍርድ ቤት ቅጣትን በመሰለው የሚያቀልባቸው የወንጀል ህግ አንቀጾች የትኞቹ ናቸው።
14.ተደራራቢ ወንጀሎችን አይነት ዘርዝር።አንድነት እና ልዩነታቸውስ።
15.ልዩ የቅጣት ማክጃ እና ማቅለያ የሚባሉት የትኞቹ ናቸው።
16. በወንጀል ስነስርአት ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮችን ዘርዝር
17.የአስተዳደር ውል እና መደበኛ ውል ልዩነት።
18.እዳ ሚከፈልበት ጊዜ ቅደም ተከተሉ.....ማለት ለሰራተኛ

18.እዳ ሚከፈልበት ጊዜ ቅደም ተከተሉ.....ማለት ለሰራተኛ የሚከፈል፣ለግብር የሚከፈል፣ለቀለብ የሚከፈል የቱ ይቅደም።
19.ለውርስ ያልተገባ መሆን እና ከውርስ መነቀልን አብራራ።
20.የቅጣት ይርጋ እና የክስ የርጋን በወንጀል አብራራ።
21.ከውል መፈጸም ጋር በተያያዘ ተዋዋዮች በተናጠል ውል መሰረዝ(unilateral cancelations) የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ምድናቸው።
22.በሰውር የተደረገ ይዞታ እና በማያሻማ አይነት የተደረገ ይዞታ ልዩነት እና አንድነት።
23.የመልካም ጸባይ ዋስትናን መርህን አብራራ።
24.የወንጀል ህግ ግብ እና አላማ አስቀምጥ።
25.ክስ ወደሌላ ስፍራ የሚዛወርባቸው ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው።
26.በጋብቻ እና እንደ ባልና ሚስት መኖር ያላቸው አንድነት እና ልዮነት።
27.በፍርድ መከልከል እና ህግ መከልከል ልዩነት እና አንድነት።
28.ጋብቻ ከፈረሰ በኃላ አንዲት ሴት 180 ቀን ሳይሞላት ማግባት የምትችለው መቼ ነው።
29.ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችን ዘርዝር።
30.ጋብቻ የሚፈርስባቸው 4ቱ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው። ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ የሚኖረውን ውጤት ዘርዝር።
31.ለውርስ ያልተገባ ሰው ሟችን ሊወርስ የሚችልበት exceptions ምድን ናቸው።
32.አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው ለግዴታው መኖር ማስረዳት አለበት(one who alleged the fact has to proof it)ለሚለው የህግ መርህ በወንጀልም ይሁን ፍትሐብሮር ያሉ exception ኖችን ዘርዝር።.....ለምሳሌ የውርስ ህግ 896፣ የወንጀል ህግ 35።
33.ፍርድ ቤት አንድን ሰው ጥፋተኛ ካለ በሓላ ከቅጣት በፊት ወንጀሉ በይርጋ የቀረ መሆኑን ቢያውቅ መዝገቡን በይርጋ መዝጋት አለበት ወይስ በይግባኝ ነው ሊታረም [illegible]